# ይድረስ ለአራዳ ልጆች- ተጻፈ ከባሕር ማዶ ወገኖቻችሁ

የሰማዕቱን የብፁኡ አቡነ ጴጥሮስን ወኔ ወርሳችሁ፤ የአራዳን ሐዋርያ የይድነቃቸው ተሰማን "ድጓ-አራዳ" ቀስማችሁ፤ የአብሮ መኖር፤ የመተዛዘን፤ የመከባበር፤ የፍቅር፤ እንዲያው በደምላላው የሥናይ ማህበራዊ ህይወት ደቀ-መዛሙርት ስለ መሆናችሁ ድፍን ኢትዮጵያ የመሰከረላችሁ! አቀናቃኙም ሳይቀር፦ « መገን ያራዳ ልጅ እንደ ድንጋይ ኳሱ! ከምኔው ተጮሆ ከምኔው ደረሱ ...!» በማለት ለወገን ደራሽነታችሁን የተቀኘላችሁ፦

ውድ የአራዳ ልጆች ሆይ! እንደምን ከርማችሁልናል? እኛ ከእናንተ ናፍቆት በስተቀር በወንዛችንም ባይሆን በሠላማችን አለን።

ውድ የአራዳ ልጆች ሆይ! ይህን ደብዳቤ የምንጽፍላችሁ የባህር ማዶ ወገኖቻችሁ መሆናችንን በደፈናው የገለጽነው፦ ገሚሱ ከባሌ፡ ገሚሱ ከጉለሌ፡ ገሚሱ ከባቢሌ ፡ ገሚሱ ከአሶሳ፡ ገሚሱ ከአዋሳ፡ ከሚሱ ከድሬ፡ ገሚሱ ከአቧሬ፡ ብቻ ሁሉም ሁሉም ከሃገሩ እንደፈንዲሻ እየተፈናጠረ የወጣ ይመስል ከኢትዮጵያችን የተለያየ ክፍል የመጣ በመሆኑ መልዕክታችንን እንደናተ "የዕገሌ ልጆች መልዕክት" ብለን የምናስረበት አንድ ቃል አጥተን ነው። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያዊነታችን አንድ አድርጎን፤ ባህር የዘለቀው ዜግነታችን አቆላልፎን ፤ እንደ አራዳ ልጆችም ባይሆን ፍቅር አለን። የኛን ነው የምንላችሁ..! ሌላውማ..! እንኳን ሊፋቀር የመጣበትን ወርጅኑን ረስቶ ፤ እነጣ ብሎ ገረጥቶ ፤ተሁለት አጥቶ፤ ይነሆልላል።

ውድ አራዶች ሆይ! ይህን ደብዳቤያችንን አቅም ፈቅዶ ጀማው ከተሰየመ በተክዚና፤ ያም ካልሆነ በትግስትና በጥሞና እንደምታነቡት ተስፋችን ነው። ባይሆን እንደ ስልኩ የበርጫ ኮሌክት ኮል ካለ ሂሳቡ በኛ ይሁን!፤

በነገራችን ላይ፦ የሁላችንንም ሃሳብ ጨምቀህ ፤ አርቅቀህ፤ በምታውቀውና አራዶች በሚገባቸው ቋንቋ ጻፍ ብለውኝ እየጻፍኩ ያለሁት ጌታቸው መኩቴ እባላለሁ! የዛሬውን አያድርገውና ድፍን አቧሬንና ከፊል 4ኪሎ፦ ከእንሳሮ እስከ ቤልኤር፤ ከጥይት ቤት እስከ ግቢ ገብርኤል፤ ሰላም ወዳዱን በሰላምታ፤ ጥጋበኛውን በቴስታ ፤ ሳስተናግድ የቆየሁ አንቱ የተባልኩ ነበርኩ። በኔ ቴስታ የተመታ ሰው ያለማጋነን በትንሹ 2 ሰአት ያሸልብ ነበር። በኋላ ጌቾ መራጂ- ቴስታው አንሲቲጃ! የሚል ቅጽል ስም አወጡልኝ። መራጂ መዶሻ አይደል? አኒስቲጃም ማደንዛዣ ነው። ቴስታው አደንዛዥ ማለታቸው ነው። አሁንም ወደ እንሳሮና ቤልኤር ጎራ ብላችሁ ጌታቸው መኩቴ ብትሉ የሌለውም ቢሆን ተበድሮ ይጋብዛችኋል። ለኔ ካለው ፍቅር። ብቻ አንዳንድ ስም አጥፊዎች ጌታቸው መኩቴ ስትሏቸው ፤ ጌታቸው ሙኩቴ ሊሏችሁ ቢችሉ አትገረሙ።ቅናት ነው። ቦዲ ቢልደር ስለነበርኩ፤ የሚቀኑ ነበሩ። በሉ የራሴን ጉዳይ ስዘረዝር እዚህ ያሉት ጓደኞቼ እያፈጠጡብኝ ነው ወደ ጋራው መልዕክታችን ተመለስ ዕያሉ፦ልመለስ።

ውድ የአራዳ ልጆች ሆይ! ፦ በዲበኩሉ በኩል የላካችሁትን "ምሬት-የተቀላቀለውን" መልዕክታችሁን አነበብነው ብቻ ሳይሆን ተጎነጨነው ነው የሚባለው። እናም ስሜታችን እጅጉን በመነካቱ፤ ይህን አስቸኳይ መልእክት እንድንጽፍ ተስማማን። ሃዘናችሁ አሳዝኖናል! ጭንቀታችሁ አስጨንቆናል! ስጋታችሁ አስግቶናል!። ለሁላችንም የሚበቃ አንድ ጀንጥላ ማጣታችን የኛም የዘወትር ቁጭት ነው።

አዎ! ሕብረት ሲሉን ህብረት ስንል፤ ቅንጅት ሲሉን ቅንጅት ስንል፤ አንድነት ሲሉን አንድነት ስንል፤ እንዳው ብቻ በተስፋ የተከተልነው ተስፋ ሁሉ ለፍሬ ሳይለው፡ በመከፋፈል ሾተላይ እየተጠናፈር፤ እንዳሳቀቀን እዚህ ደረስን። ዛሬም ሌላ ተስፋ ታቅፈናል፡፡ ትብብርን አመልካች ቃሎች አለቁ መሰለኝ ዘንድሮ ደግሞ በመድረክ ልንሞክር ነው፦ ለፍሬ ካለው።

ውድ የአራዳ ልጆች፡- ብሶታችንን መረር ፤ ከረር ያደረግነው ገራገር ቋንቋ ጠፍቶን ሳይሆን፤ እንዲያው ባህር ማዶ በመሆናችን ብቻ የናንተን የወገኖቻችንን ስሜት የዘነጋን እንደመሰላችሁ ከመልዕክታችሁ በመረዳታችን ነው። በርግጥ የዘነጉም አሉ! እኛ ግን አሁንም እትብታችንን የቀመሰው አፈር ጠረኑ ታፍንጫችን ያልጠፋ መሆኑን በምትወዱቸው በአቡነ ጴጥሮስና በአራዳው ጊዮርጊስ ምለን እናረጋግጥላችኋለን።

የአራዳ ልጆች ሆይ፡-በነገራችን ላይ፡ ከላይ ያሉትን 2 አንቀጾች የጻፍኩት እኔ የአቧሬው ጌቾ መራጃ-ቴስታው አኒስቲጃ አይደለሁም፡፡ ስሜታችሁ ስሜታችን መሆኑን እንድትረዱ! ስጋታችሁ ስጋታችን መሆኑን እንድታውቁ፡- በሃዘን ጠለቅ፤ በብሶት ደመቅ፤ በስጋት ደፈቅ ብሎ ስሜት ሰቅሰቅ ያሚያደርግ ፤ መልዕክት እንዲጻፍ በተስማማነው መሰረት፤ ተመሃላችን በመርጦ ለማሪያም ገዳም የቅኔ ተማሪ የነበረውን የቀድሞውን "የኔታ" የዛሬውን ጓደኛችንን በወርጅናል አማርኛ አንተ ጻፍ ብለነው የተበተበው እሱ ነው። ለኮፒ ራይትም ቢሆን ማሳወቅ አለብኝ ብዬ ነው፡፤ መራር ከራሩን ጣፊው ክንዴ ደምመላሽ ይባላል ተዋወቁ።

ክንዴ ብሶት አበዛ መሰለኝ፡? ብሶት የወለደው ሰራዊት ለ19 ዓመታት ብሶቱን ሁሉ አራግፎበት እሱም ያራግፈው እንጂ ምን ያድርግ ትላላችሑ? ለማንኛውም እስኪ ወደ ቁምነገሩ እንግባ፡- ውድ የአራዳ ልጆች ሆይ! በዘንድሮው ምርጫ የእንስቲቷን አንበሳ፤ የብርትኳን ሚደቅሳን አላማና አርማ አንግበናል የሚሉትን ወገኖች ልትመርጡ መዘጋጀታችሁን ስንሰማ በጣም ተደሰትን። ወደሽ ? አሉ! እትዬ አልታዩ፡- ሌላማ ምን አማራጭ አለ? ለማንኛውም እስኪ መጀመሪያ መራጭና ተመራጭ በሰላም ይገናኙ። ተያም በኋላ ኮሮጆው ከገመሬ ቀማኛ ድኖ በሰላም ውሎ ይግባ!!

አራዶች ሆይ! የብርትኳን ሚደቅሳ ጉዳይ ከኛም አልፎ አለማችንን እያስደመመ ያለ ጉዳይ ሆኗል። ይህን ደብዳቤ ለናንተ በምንጽፍበት ደቂቃ እንኳ ታዋቂው አሜሪካዊ አርቲስት Chris Flaherty ፕሬዘዳንት ኦባማ ለብርትኳን የህሊና ዕስረኝነት እውቅና እንዲሰጡ በመጠይቅ፡- ጥያቄውም ምላሻ እስኪያገኝ በዋይት ሃውስ ቤተመንግስት ፊት ለፊት የረሃብ አድማ እያደረገ ይገኛል። መቼም እናንተም ሳትሰሙት አትቀሩም ፡፡ የክሪስ ተግባር በተለይ ኢትዮጵያዊ ሆኖ የሃገሩንና የሕዝቡን ብሶት ችላ ያለውን ዜጋ ሁሉ አሸማቋል! አሳፍሯል! አንገት አስደፍቷል። እኛን መሰል ወገን ደግሞ ጮቤ አስረግጧል። እናም የብርትኳን ጉዳይ በምኒሊክ ቤ/መ የሰፈሩትን ገመሬዎች እንቅልፍ እየነሳ እንደሆነ እየሰማን ነው።ታስራም የምታስጨንቅ አንበሳ!

የሚገርማችሁ ነገር እዚህ የሚገኘው፡- ተቃዋሚውም፤ ችካል አደሩም፤ ለዘብተኛውም ፤ ዋትስ አፑም ሁሉም ሁሉም የሚስማማበት አንድ ነገር ቢኖር በብርትኳን የህሊና ዕስረኝነት ላይ ነው፡፤ ከፋፋይና ነገር መታሪ ሽብልቆች እንደ አሸን በፈሉበት፤ አንድ የሚያደርግ ፤ የሚያስማማ፤ አንድም ነገር በጠፋበት ጥፉ ዘመን ፤ እሷ መገኘቷ ያለምክንያት ነው ትላላችሁ? አዎ! መታሰሯም ለበጎ ሳይሆን አይቀርም።

እዚህ ያሉ ጓደኞቼ ማሳሰቢያ አለን እያሉኝ ነው፡- "ችካል አደር" የሚለው መጠሪያ ለአራዳ ልጆች አዲስ ሊሆን ስለሚችል፤ አብራራላቸው የሚል ነው ማሳሰቢያው! ጥሩ ላብራራዋ!፡- አዎ እዚህ ! "ችካል አደር" የምንላቸው ወደ ሃገር ቤት ሄደው ትንሽ ካሪ ሜትር አስቸክለው ከመጡ በኋላ ከተቃዋሚነታቸው ታቅበው ድራሻቸው የሚጠፋውን ነው፡፤ እነኚህ ወገኖች ናቸው፡ የወያኔን በደል ለመቃወም በሚደረግ ሰልፍ ላይ ፤ ቀሩ እንዳይባሉ ዱቤ ከልል ባርኔጣና መነጽር ደንቅረው በቴሌቪዥን መስኮት የምታይዋቸው። እኛማ ማንን ፈርተን?ተተተ። እናም ውድ ያራዳ ልጆች ሆይ! ወቀሳችሁ! ምሬታችሁ! ሃዘናችሁ! በነዚህ ከንቱዎች ከንቱ ተግባር የተነሳ መሆኑን እንድታውቁልን እንሻለን።

ታሪክና ግዜ ሲፈቅድ ያስቸከሉትን ብቻ ሳይሆን የጠቡትንም መትፋታቸው አይቀርምና አይዟችሁ! ኢትዮጵያ ደካሞችም ብርቱዎችም ወልዳለች። ጫሚሶም ብርትኳንም የኢትዮጵያ ልጆች አይደሉ? የናት ሆድ ዥጉርጉር ....ብቻ ምንም ይሁን

ምን ቀፈቱን ለመሙላት ብሎ! የወገኑን ጩሀት ችላ ያለ ሁሉ! የሥራውን ማግኘቱ አይቀረም አትጠራጠሩ።! የደም እዳ ይዘግይ እንጂ መከፈሉ እንደሁ አይቀርም!

አራዶች ሆይ! ለመሆኑ የሕዝቡ ስሜት እንዴት ነው? መቼም እንደ ምርጫ 97 እንደማይሆን አይጠፋንም። አቤት አቤት!!!! የምርጫ 97 እኮ ገሪም ነው። በተለይ ሚያዚያ 30 ቀን የተደረገውን ሠላማዊ ሰልፍ ስናስታውስ ዛሬም ውስጣችን ይንተከተካል!..ድፍን መርካቶ ሸራውን ጠቅልሎ ፤ ድፍን ሽሮሜዳ ድርና ማጉን ሰቅሎ! ድፍን 4ኪሎ ፤6ኪሎ፤ ፒያሳ፤ ዶሮ ማነቂያ፤ ሰራተኛ ሰፈር፤ ተከርቸሙን ቀርቅሮ! ድፍን ቄራና ሾላ ከብትና በጉን ጠፍሮ! ድፍን ኳስ ሜዳ፤ ጃንሜዳ፤ ካምቦሎጆ፤ ቅሪላውን አሸቀንጥሮ!….ብቻ ሁሉም ሁሉም አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኖ የተመመበት! የልቡን መሻት የገለጸበት ፤ ስልጡንነቱን ያሳየበት ሰልፍ ነበር እኮ!።

እውነት እውነት እንላችኋለን የአራዳ ልጆች፡- የአራት ኪሎዎቹ ገመሬዎች በዛን ግዜ ሽንፈታቸውን በጸጋ ተቀብለው ቢሆን ኖሮ ከማንም በላይ በዚያ በመሰለ የታሪክ አንጸባራቂ ፈርጥ የሚያኼጡት እነሱ ነበሩ። በታሪክ ሰሪነታቸው ብቻ በዘንድሮው ምርጫ ሕዝብ እነሱን ይመርጥ እንደነበር አትጠራጠሩ ።አላለላቸውም! እዋይ! እዋይ! ካብዚ መሰል ትህትና አይፈልጾም!

እስኪ ደግሞ ቦለጢቃውን ጋብ እናድርግና የኛን የባህር ማዶ ሕይወት ጨለፍ አድርገን እናቃምሳችሁ።

ከላይ እንደገለጽነው ከተለያየ የኢትዮጵያ ክፍል የመጣን በመሆናችን ቅኝታችንም እንደዛው ነው። “ባምባሰል ቅኝት ባቲ አይመታም” እንዲሉ፡- 10 አመት አብረህ ኖረህም የማትግባባው ይኖራል። አብዛኛውን አንድ የሚያደርገው ግን ምን መሰላችሁ? ቲዮታ ካምሪ ። ተዘወሪ ተዘወሪም ..በቶዮታ ካምሪ ነው! ….ኒዴማ! ኒዴማም! …በቶዮታ ካምሪ ነው! … ልወዝወዘው..ልወዝወዘው…በቲዮታ ካምሪ…ብቻ ሁሉም ሁሉም…ፏዋ ፏዋ ይላል ካምሪ….ነው።!

ኑሯችንም እንደ ጸባያችን ይለያያል! ጠንካራው በትምህርቱ ገፍቶ፤ የነጭ አልቃ ሆኖ ኮርቶ ያኮራሃል። ትምህርትም ዕጣ ክፍሉ ያልሆነም EBCA ይገባል። EBCA ማለት የካሳ ገብሬ Ethiopian Building Construction Authority መስሏችሁ እንዳትሸወዱ፡፡ EBCA ማለት Every Body Can Apply የተሰኘ ሆደ ሰፊ፤ ሁሉን አቃፊ፤ ለመቀጠር ፊደል መቁጠር ሳይሆን ሰው ሆኖ መፈጠር ብቻ! የሚያስፈልገው የሥራ ዘርፍ ነው፡፤ የሥራው አይነት ሊለያይ ይችላል፡፤ አሌሌ!!!! ሁሉ አለ …በያይነቱ ሞልቷል። አበሽ ግን ያው "እንቢኝ" ማለት ከደም አይደል? የነጭ አለቃ ጠልቶ አብዛኛው የራሱ አለቃ ሆኖል "በታክሲ-ሽቁ" ተሰማርቷል። እየጫነ እያወረደ! ቅቡ….!እየጫነ እያወረደ! ቅቡ….ነው!! ዘለለትነ ህይወቱ እንደዚህ ነው..!.....

በኛ በኩል ሌላው ሁሌም የሚያሳስበን በባዕድ ሃገር ተወልደው የሚያድጉት ልጆቻችን ጉዳይ ነው። ይህን ስንል መቼም በላይ በላይ ከተወለዱት የአራዳ ሰፈር ሕጻናት ሕይወት አኳያ መዝናችሁ፤ ደግሞ የታደሉ ልጆች ውጭ አገር ተወልደው ምን ያሳስባችኋል? እንደምትሉ እናውቃለን! በርግጥ በብዙ ነገር የተሻለ ሕይወት ስለሚኖሩ እግዚአብሄርን እናመስግነዋለን!፡፡ ያም ሆኖ ግን ስለ ተተኪ ትውልድ የማንነት ጥያቄ ጠለቅ ብለን ስናስብ ያስፈራናል፡፤ ግብግብ የያዝነውም ልጆቻችን ቋንቋቸውንና ባህላቸውን አውቀው እንዲያድጉ ለማድረግ ነው፡፤ አንዳንዱ ደግሞ የሰለጠነ እየመሰለው ልጆቹን እቤትም ውስጥ በእንግሊዘኛ ያናግራል።ይለማመድባቸዋል ማለቱ ይቀላል፡፤ እኛን መሰሉ ደግሞ ቢቻል ቅኔም ለማስተማር ይፈልጋል። ትንንቅ ነው የያዝነው። ልጆቹ ደግሞ እንዴት ፈጣኖች መሰሏችሁ፡?

በቀደም እለት የጓደኛችን የ7 ዓመት ልጅ ያለችውን ብትሰሙ አታምኑም፡፡ ጓደኛችን የአባባ ተስፋዬን ተረት በቪዲዮ አገኘና ልጁ አማርኛ በደንብ ስለምትችል እንድታየው ይከፍትላታል፡፤ አባባ ተስፋዬም ሁሌም ተረት ከመጀመራቸው በፊት እንደሚያደርጉት፤ ልጆች አባትና እናታችሁና ታላላቆቻችሁ አክብሩ፤ ጥሩ ልጅ ሁኑ እያሉ ሲመከሩ ፤ የሰባት አመቷ ልጅ ምን እንዳለች ታውቃላችሁ? Stop your bla bla … go to your story if you have one! ታዲያ ይሄ

የሚታመን ነው አራዶች ? እኛ 9 ና 10,11 ዓመት ሆነንም አባባ ተስፋዬን እንዴት አፋችንን ከፍተን እንዳምጥ እንደነበር ስናስታውስ የዘንድሮ ልጆች ነገር ያስፈራናል። ገራገሩ የልጅነት ወቅት ከተፈጥሮ ማህደር የተሰረዘ ይመስላል። እንግዲህ ውሎና አዳራችን ከብዙው በጣም በጥቂቱ ይህን ይመስላል! ሌላው ሌላውማ ለማን ይነገራል.....ያራዳ ልጆች እንደ ጥልዬ ሆድ ይፍጀው! ብለን ብናልፈው ይሻላል።!

በነገራችን ላይ አራዶች ሆይ! ዲበኩሉ የሚባለው ወዳጃችሁን ልንተዋወቀውና ስለ ዝርዝር ጤንነታችሁ ልንጠይቀው ያለበትን አጠያይቀን፤ በካምሪያችን አገር ሰንጥቀን፤ ብንሄድ ልናገኘው አልቻልንም።ጠላታችሁ ዝግት ይበልበት! በሩ ጥርቅም ብሎ ተዘግቶ ደረስን።

የበሩን አዘጋግ ያስተዋለው ያቆሎ ተማሪው ጓደኛችን ክንዴ፡- “አዬ ይሄ ሰው በቅርብ ያለም አይመስል ዘግቶ ከሄደም ሰንበት ሳይል አይቀርም” ቢል፡- ሁላችንም በአንድ ድምጽ፤ በምን አወቅክ? ብለን በጥያቄ አጣዳፍነው፡- ይኸውላችሁ በጣሳ ያለው አትክልት አፈሩ ተአለት ገሯል! ውኃ መች አግኝቶ ያውቃል! ሲለን እኛ ከተማ ቀመሶቹ በሳቅ ሞትን ፡፡

ለካስ አጅሬ የቆሎ ተማሪ ሳለ ለቃረማ በር ተ በር ሲወናጨፍ ባገኘው የበሮሎጂ እውቀቱ ተጠቅሞ እንቅጩን ነበር የነገረን፡፤ እንዳለውም ወዳጃችሁ ዲበኩሉ ከቤቱ ከወጣ 15 ቀን አልፎታል አሉን አንድ ጭንብስብስ ያሉ የፈረንጅ አሮጊት ጎረቤቱ ። ግቡና ጠብቁት አይነት ትህትና መቼም እዚህ አገር እንደሌለ ታውቃላችሁ...በወሬ ወሬም ቢሆን። የኛ ባህል እኮ ወርቅ ነው። ሰው ፈልጎ ያጣ እንግዳን ግቡና ጠብቁት ብለን እናስተናግዳለን። እዚህ እንደዛ አይነት ነገር የለም። ብቻ አሾሉቆ በቀዳዳ ያይሃል፡፤ ይህችም አሮጊት ስታሾልቅ አይተናት ደንግጣ ነው የነገረችን።

በኋላም አይ እንግዲህ ምን እናድርግ? ከ15 ቀን በፊት የወጣ ሰው መቼ ሊመለስ እንደሚችልም አይታውቅምና፤ ወደ መጣንበት እንመለስ ብለን ወደ ካምሪያችን ስናመራ፤ አንድ ሌላ ካምሪ አጠገባችን መጥቶ ቆመ። የኛው ሰው መሆኑን አልተጠራጠርንም፡፤ እንዲያውም ዲበኩሉ እንደሆነ እርግጠኛ ሆነን ሳለ፡- ወጣት አይሉት ለአመል ጸጉር ባናቱ የሌለ ፤ ጎልማሳ አይሉት እንደ ፍንዳታዎች ሎቲ ጆሮና አፍንጫው ላይ ያንጠለጠለ፤ ደረታም ሰው ከመኪናው ወጥቶ እየነጠረ ሰላምም ሳይለን  በአጠገባችን አልፎ ወደ ሕንጻው ሲያመራ፡ ከመሃላች ደፋሩ ክንዴ፡- ወንድም ኢትዮጵያዊ ነህ ? ዲበኩሉ ነህ..? በማለት አከታትሎ ይጠይቀዋል።

ሰውየውም! Yap  am from Ethiopia!  አለና አማርኛ በማያውቅ መንፈስ መለሰልን፤ የቆሎ ተማሪው ጓደኛችን ደሙ ፍልት ብሎ፡-  አንተ የተናገርከው እንግሊዘኛ እኛ የሚያቅተን መስሎህ ነው? በሚል ስሜት  አር ዩ ዲበ ኩሉ? ብሎ በጥያቄ ያፈጥበታል፡፤ ሰውየውም መልሶ Oh! you mean straight D? No I am not. I have n't seen him for a while sorry!" አለን። straight D! ያለው ነገር ግራ ገብቶን ስንተያይ፤ አሁንም የቆሎ ተማሪው ጓደኛችን በንዴት መልሶ " እኔ ምለው አማርኛ አትችልም? ሲለው፡-

ሰውየውም ቅልጥፍ ባለ አማርኛ አይ ትንሽ ላካብድ ብዬ እንጂ እችላለሁ ሲለን ሁላችንም በሳቅ ፈነዳን። ለካስ እሱም ሌላው  የአራዳ ሰፈር ጉድ ኖሮ ፤ ወዲያው ተግባብቶን፤ አረፍ ብለን ሻይ ቢጤ ቀማምሰን እንድንሄድ ጋበዘንና ወደ ቤቱ ገባን። በኋላም  straight D ያለውን ነገር አንስተን ጠየቅነው። አብራርቶ ሲነግረንም፤ እውነት እውነት እንላችኋለን በአራዳ ልጆች ስም አወጣጥ እጅግ ተደነቅን። ለካስ "ዲ በኩሉ" ያላችሁት በማትሪክ ሁሉንም ሳብጀክት D በማምጣቱ ነበር? ዲ በኩሉ.....ወይ ስም አወጣጥ!!! እዚህ ደግሞ "straight D" ይሉታል። ወይ ገሪም!  የትም ተወለድ አራዳ እደግ የሚባለው ለካስ ለዚህ ነው?

የቆሎ ተማሪው ጓደኛችን ክንዴ ደግሞ የለም ቃሉ ግዕዝ ነው! አሁን ዘንግቼው እንጂ ቃሉ ግዕዝ ቃል ነው ብሎ ሙግት ቢገጥመን፡ ይሄው የዲበ ኩሉ ጎረቤት የአራዳ ጮሌ፤ ምን አለ መሰላችሁ፡- አዎ! ልክ ነው ቃሉ ግዕዝ ነው ፡፤ ግዕዙ ግን

የሰማዕቱ የአቡነ ጴጥሮስ ገዳም የአራዳው ጎርጊስ ግእዝ ነው ብሎ በሳቅ ገደለን፡፡ ዲበን እስክናገኘው ቸኩለናል፡፡ ዲበ ግን የሄደበት አለመታወቁ ቢያሳስበንም ጎረቤቱ ምንም አይሆን የሄደበትን ባልነግራችሁም አውቃለሁና አትስጉ ብሎናል፡፡ እናንተም ስጋት አይግባችሁ የአራዳ ልጅ መግቢያና መውጫው ብዙ ነው....ከአውሬም ተስማምቶ መኖር እንደሚችል ለናንተ አይነገር መቼም፡፡ በሉ እንግዲህ እኛም ወደ መጣንበት ከተመለስን ብኋላ ነው ይህን ደብዳቤ ጥፈን የሰደድንላችሁ፡፡

ከዲበ ኩሉ ጋር ብንተዋወቅ ደስ ባለን ነበር! እግዚአብሄር ባለው ቀን ይሆናል እንግዲህ !በሉ አራዶች ሆይ እናንተም በርቱልን ! ምርጫውም የቀረው ጥቂት ቀን ነውና ከቻላችሁ ከምርጫው በፊት ድባቡን ጻፉልን፡፤

የባህር ማዶ ወገኖቻችሁ

ገር ገሩን ጣፊ ጌታቸው መኮቴ (የአቧሬ ሰፈር የቀድሞ ጠርናፊ )

ከራር መራሩን ጣፊ ክንዴ ደመላሽ (የመርጦ ለማሪያም ገዳም ምሩቅ)

የተረሳ፡- ክንዴ አራዳ ማለት ምን ማለት ነው? ሲል የአራዳውን ጀማ ጠይቋል፡፡ጥያቄው ዋዘኛ አይመስለኝምና እስኪ አብራሩለት፡፡ እኔ ለግዜው ከአስናቀች ወርቁ ዘፈን ላይ ኮርጄ አራዳ ማለት ለሰው አዛኝ፤ሩህሩህ ማለት ነው ብዬዋለሁ፡፤ ታጠፉሁ አርሙኝ፡፡